# የባንክ አመጣጥ በኢትዮጵያ

ካሣ ዘለቀ፤ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ



ሰው ልጅ ታሪክ የተለያዩ ትውልዶች ባህል፣ ሥልጣኔና ዘመን ተከታታይነት ያለበት ነው፡፡ ለአሁኑ መሠረት የሚጣለው ባለፈው፣ ለወደፊቱ ደሞ በአሁኑ ነው፡፡ ዛሬ አገራችን የደረሰችበት የዕድገት ደረጃም ምን ያህል እንደሆነ ለማጣጣም የሚቻለው ወደ ኋላ መለስ ብለን በያንዳንዱ አቅጣጫ ያለውን የሥራ እንቅስቃሴ ከአሮጌው ጋር ማነጻጸር ስንችል ነው፡፡

በሀገራችን ታሪክ ውስጥ ከመሪዎች እስከ ተራ ሰዎች ለሀገራቸው የሠሩትን ለማወቅ ስንጥር የሥራቸው ውጤት በታሪክ ሠፍሮ ዘላለም ሲወደሱ የሚኖሩ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም መካከል አፄ ምኒልክ አንዱ ናቸው፡፡ አፄ ምኒልክ ሙሉ ሕይወታቸው ሲነበብ አገራቸዉን ለማሠልጠን ከሁሉ በፊት የሥልጣኔ ባለቤት ከሆኑት ከፈረንጆች ጋር መቀራረብ የፈጠሩ ባገር ውስጥ የሚገኘውን የተለያዩ ማኅበረሰብ ከቆላም ከደጋም፣ ሴቱንም ወንዱንም፣ እስላሙንም ክርስቲያኑንም፣ ሽማግሌውንም ወጣቱንም በማስተባበር ግዛታቸውን ባንድ አገርነት ያቆሙና ወደ አንድ የታወቀ የሰላም አኗኗር በመምራት ለዛሬው የጋራ ማንነታችን ዋነኛወን መሠረት የጣሉ የታሪክ ባለውለታ እንደሆኑ ሁላችንም እንረዳለን፡፡

በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በሀገሪቱ ከተዘረጉ የሥልጣኔ አውታሮች ውስጥ አንዱ የባንክ ሥራ መጀመር ነው፡፡ ሥራው እንዴት ሊጀመር ቻለ? የአሠራሩ ሁኔታስ እንዴት ነበር? የሚሉትንና ሌሎቹንም ከማስከተሌ በፊት በዓለም ደረጃ የባንክ ሥራ እንዴት ተጀመረ? የሚለውን በመጠኑ እንመልከት፡፡

የባንክ አጀማመርን በሚመለከት ጣሊያኖች የቅድሚያ ተጠቃሾ ናቸው፡፡ የቃሉን አመጣጥ ራሱን ስንመለከት የመካከለኛው ዘመን እንግሊዝኛ 'Bank' የሚለውን አጠራር ከመካከለኛው ዘመን 'Banque'፣ ከዚያው ዘመን ጣሊያንኛ 'Banca' እና ጀርመንኛ 'Banc' የሚል ቃል እንደተዋሰ ዊኪፔዲያ የተሰኘው የመረጃ ድረ ገፅ ይገልጻል፡፡ የቃሉ ትርጉምም አግዳሚ ወንበር ወይም ገንዘብ ከፋዮችና የእንግዳ አቀባበል ባለሙያዎች እንግዶቻቸውን የሚያስተናግዱበት ጠረጴዛ መሆኑን ይሄው ድረ ገፅ ይጠቁማል፡፡

የባንክ አመጣጥ በዘመናዊነቱ ሊጠቀስ በሚችል መልክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለማችን ብቅ ያለው በዘመነ ህዳሴ (Renaissance) ነው፡፡ በዚያን ዘመን በጣሊያን ውስጥ በሀብታምነታቸው ይታወቁ በነበሩ እንደፍሎረንስ፣ ቬኒስና ጄኖዋ ከተሞች እንደተጀመረ ይነገራል፡፡ የዚያው ዘመን የሥነ ጽሑፍ ጠቢብ ዕውቁ ሼክስፒር ‹የቬኑሱ ነጋዴ› በሚል ርዕስ ድርሰት የጻፈው ለዚህ ሣይሆን ይቀራል? ለማንኛውም በዚያን የ14ኛው ምዕተ ዓመት የሬነሰንስ ዘመን በፍሎረሰንስ ታዋቂ አበዳሪና ገንዘብ አስቀማጭ የነበሩ ባርዲና ፔሩዚ የተባሉ ቤተሰቦች የሀገራቸውን የባንክ አሠራር ወቅቱን በሚመጠን ሁኔታ ከማዘመናቸውም በላጣሊያንን አልፈው በአውሮፓና በሌሎች ግዛቶች የባንክን ጠቀሜታ እያስተዋወቁና እየሠሩም እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ (ዊኪ ፔዲያ)

በርካታ ታሪካዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ቀደም ሲል በባንክ የመገልገል መሠረተ ሀሳቡን ለዓለም ያበረከቱት ወርቅ አንጣሪዎች ናቸው፡፡ ወርቅ አንጣሪዎች ወርቃቸውን የሚያስቀምጡበት ጠንካራ ሣጥን ስለነበራቸው ከብርና ከወርቅ የተሠሩ ጌጣጌጦችንና ሌሎችንም ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎች በአደራ ንብረትነት እየተቀበሉም ያስቀምጡ ነበር(Keep Interest Money):: ወርቅ አንጣሪዎች ወርቅ ላስቀመጡ ለባለ ንብረቶች ደረሰኝ ይሰጣሉ፡ ለሰጡትም አገልግሎት መጠነኛ ክፍያ ያስከፍላሉ፡፡ ይህ ባህል (Tradition) ተጠናክሮ ቼክን በዘመናችን ገንዘብ ለመክፈል እንደምንገለገልበት ሁሉ ወርቅ አንጣሪዎች ለደንበኛው የሚሰጠውን ደረሰኝ ለተመሳሳይ ሁኔታ ተገለገሉበት፡፡ ለምሳሌ ሁለት ሰዎች በአንድ ወርቅ አንጣሪ ዘንድ ገንዘባቸውን

ቢያስቀምጡ ለወርቅ አንጣሪው ማስታወሻ በመጻፍ ከአንደኛው ግለሰብ ተቀማጭ ተቀንሶ ወደ ሌላው ተቀማጭ እንዲዘዋወር ያደርጉ ነበር፡፡ በዘመናችን የምንገለገልበት ቼክም ከዚሁ ማስታወሻ የአሠራር ሥልት የተወረሰ ነው፡፡ ይህ ማስታወሻ የሚከተለው ይዘት ነበረው፡፡

ለሚስተር-------ወርቅ አንጣሪ
እባክዎትን ለሚስተር ------ ይክፈሉ
የብር መጠን ------
ፊርማ----(የከፋይ)

ይሁን እንጂ ከረዥም ጊዜ በኋላ አገልግሎት እየከፈሉ የተከበሩ ዕቃዎችን የሚያስቀምጡ ሰዎች በጣም ጥቂቶች መሆናቸውን ወርቅ አንጣሪዎች ተገነዘቡ፡፡ ስለዚህ ወርቅ አንጣሪዎች የአደራ ገንዘብ በማስቀመጥ ለሰጡት አገልግሎት ያስከፍሉ የነበረውን መጠነኛ ያገልግሎት ክፍያ አቁመው ለአስቀማጮች ወለድ በመክፈል በርካታ ደንበኞችን አፈሩ፡፡ ወርቅ አንጣሪዎችም ከተቀማጩ ገንዘብ የማይፈልጉትን ለሌላ ተበዳሪ በመስጠት ትርፍ ያገኙ ጀመር፡፡ በመሆኑም የወርቅ አንጣሪዎች ተግባር ከጊዜ ወደ ጊዜ ጎለበተ፡፡ እንግዲህ የዘመናችን የባንክ ሥርዓት በዚህ መልኩ በመጀመር ዓመታትን አሳልፎ እዚህ ደርሷል፡፡

ባንክ ማለት ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ ድርጅት ነው፡፡ ከደንበኞች ተቀማጭ ገንዘብ የሚቀበል፣ ደንበኞች ሲፈልጉትም ገንዘባቸውን የሚሰጥ፣ ለደንበኖቹ የቼክ ደብተሮችን የሚሰጥና ገንዘቡ በደንበኞች እስከሚፈለግ ድረስም ተቀማጩን አስፈላጊውን የብድር መሥፈርት ለሚያሟሉ ተበዳሪዎች በወለድ የሚያበድር ድርጅት (ተቋም) ነው፡፡

የሦሪያ፣ባቢሎን፣አቴና፣ ፅርዕ(ግሪክ)፣ፎኒቀያ፣ ምሥር(ግብፅ)፣ሮማና ኢትዮጵያ ሰዎች ለአለፉት በርካታ ምዕተ ዓመታት በባንክ ሥርዓት ይገለገሉ እንደነበር ይታመናል፡፡ የሰው ልጅ በገንዘብ መገልገል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በሌላም በኩል በባንክ መገልገል የተለመደ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በአክሱም ዘመነ መንግሥት የባንክ ሥርዓት መሠረተ ሀሳብ ሳይኖረው በባንክ የሚገለገል የሠለጠነ ኅብረተሰብ በአንድ ወቅት ተከስቶ የነበረ መሆኑ ቢገለጽ የማይታመን ይመስላል፡፡ በዚያ ወቅት ለባንክ ሥርዓት መመሥረት ዋናዉ ምክንያት ከዛሬው ጋር ተመሳሳይ ነበር የሚያሰኘው ለማኖር ፣ለመበደር እና ለመክፈል የነበረው ሥርዓት አንድ መሆኑ ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው በጥንታዊነቱ የሚታወቀው ባንክ በ1157 የተቋቋመው የቬነስ ባንክ ነው፡፡ በመጀመሪያ ሲቋቋም የዘመናችንን የባንክ ሥርዓት የተመረኮዘ አልነበረም፡፡ ይልቁንም የመንግሥት ዕዳ ለማዘዋወር(Transfer of Public Debt) የሚያገለግል ቢሮ ነበር፡፡ የዘመናችን የባንክ ሥርዓት የጎለበተው በግሪክ እና በጣሊያን አገር በ15ኛው ክፍለ ዘመን ነው፡፡ ባንክ የሚለው ቃል የተወረሰው ባንኮ(Banco)ከሚለው የጣሊያን ቃል ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል፡፡ የቃሉ ትርጉምም በአራጣ የሚያበድሩ ነጋዴዎች ገንዘባቸውን በገበያ ቦታዎች ለማቅረብ የሚያስቀምጡበት መጋዘን ማለት ነው፡፡ አበዳሪዎች የአበደሩት ሳይመለስ ሲቀር በገንዘብ እጥረት ምክኒያት የማበደሩን ተግባር ያቆማሉ (Break the Banco) በዚህም ጊዜ ገንዘብ አበዳሪዎች የባንክ ኪሣራ ደረሰባቸው ይባላል፡፡

እንግዲህ የባንክን አመጣጥ ጠቅለል ባለ መልኩ ከተመለከትን ዘንድ ወደ አገራችን ዘመናዊ የባንክ ምሥረታ ወይም አጀማመር ከመግባታችን በፊት ስለገንዘብ ዝውውር እና አሠራር ጥቂት ጥቂት እንበል፡፡ በጥንት ጊዜ የዕቃ ልውውጥ ሥርዓት ባልሠለጠኑ አገሮች ጎልቶ ይታይ ነበር፡፡ በአገራችንም ቢሆን የዚህ ዓይነቱ የመገበያያ ዘዴ መከሰቱ አልቀረም፡፡ ይሁን እንጂ ያስከትል የነበረው የዋጋ መለያየት፣ ቅንስናሽ አለመኖር፣ ከቦታ ወደ ቦታ ይዞ ለመዘዋወር አስቸጋሪ መሆን፣ ለብዙ ጊዜ ዕቃዎች ሲቀመጡ በመጠን መቀነስ ምክንያት የነበራቸውን እሴት እንደያዙ አለመቆየት እና ሌሎች ተደማምረው ችግሩን አባብሰውት ነበር፡፡ በዚያ መሀል ታዲያ እ.ኤ.አ በ1875 የፈረንሳይ አገር ተወላጅ የነበረው ተጓዥ ፔር አቮክስ (Pierre Avnoux) ከዳግማዊ ምኒልክ ጋር ተገናኝቶ በነበረበት ወቅት በዋናነት ስለገንዘብ መወያየታቸው ይነገራል፡፡ በዚያን ጊዜ የሌሎች አገር ገዥዎች እንደሚያደርጉት ብሔራዊ ግልጋሎት የሚሰጥ ገንዘብ መታተም እንደሚኖርበት አማክሯቸው እንደነበር በታሪክ ተዘግቧል፡፡ እናም አፄ ምኒልክ በ1901 በስማቸው ገንዘብ አሣትመው ሕዝቡ እንዲገበያይበት የሚከተለውን ዐወጁ፡፡

*በኢትዮጵያ የመገበያያ ገንዘብ ብር እንዲሆን የተነገረ ዐዋጅ*

*ምኣ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ*

*ምኒልክ ስዩመ እግዚአብሔር*

*ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ*

*ከዚህ ቀደም ነጋዴም ወታደርም ባላገርም የሆንክ ሰው ሁሉ በየገበያው እና በየመንገዱ በየሥፍራውም ሁሉ በጥይት ስትገበያይ ትኖር ነበር፡፡ አሁን ግን በእኔ መልክ እና ስም የተሠራ ብር፣ አላድ፣ ሩብ ፣ተሙን፣ መኃልቅ አድርጌልሃለው፡፡ በዚህ ተገበያይ እንጂ እንግዲህ በጥይት መገበያየት ይቅር ብያለው፡፡ የሚሸጥም ጥይት ከቤቱ ያለው ሰው ሁሉ እጅምሩክ እየወሰደ*

*ለጅምሩክ ሹም ይሰጥ፡፡ ጥይትም ለመግዛት የፈለገ ሰው እጅምሩክ እየሄደ ይግዛው፡፡ ይህንንም ዐዋጅ አፍርሶ ጥይት እርስ በራሱ ሲሻሻጥ እና ሲገዛዛ የተገኘ ሰው ገዢውም ሻጪውም ስለቅጣታቸው በአንድ ጥይት አንድ ብር (መቀጮ) ይከፍላሉ፡፡ ይህንንም ዐዋጅ አፍርሶ ጥይት ሲያሻሽጥ አግኝቶ ወደ ዳኛ ያመጣ ሰው በቅጣት የሚከፍሉትን ገንዘብ እኩሌታውን ለያዢው መርቄለታለው፡፡*

*ኅዳር 22 ቀን 1901 ዓ.ም*
*እንጦጦ ከተማ ተጻፈ፡፡*

አዲሱ ገንዘብ የተሠራው በብር ስለሆነ በራሱ ዋጋ ያለው በመሆኑ ጭምር በመላው ግዛታቸው በፍጥነት ያለችግር ታወቀ፡፡

**አንድ ብር፡-**
ሁለት አላድ
አራት ሩብ
ስምንት ተሙን
አሥራ ስድስት መኃልቅ ይመነዘራል፡፡

ይህም ለማንኛውም ጉዳይ በገበያ ላይ ለመገበያየት የተመቸ በመሆኑና ቢያስቀምጡት ስለማይበላሽ በሕዝብ ዘንድ በጣም የተወደደና የተፈለገ ሆነ፡፡

በ1895 ዓ.ም በዳግማዊ ምኒልክ መልክ ታትመው የወጡ ገንዘቦች ከአፄ ምኒልክ በኋላ በንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ለመንግሥትም ለድኻም የተመቸ እንዲሆን በማሰብ ቤሣ የተባለ ከመዳብ የተሠራ የብር 32ኛ ክፍልፋይ በአፄ ምኒልክ መልክ ታትመ፡፡

ይህ ቅንስናሽ ገንዘብ ታትሞ ወይም ተቀርፆ ከወጣ ከሁለት ዓመት በኋላ ደግሞ አፄ ምኒልክ ዘመናዊ ባንክ መመሥረቱን ይፋ አደረጉ(የውል ሠነዱን መጨረሻ ላይ በአስረጅነት ከቀረቡ አባሪዎች መካከል አባሪ አንድን ይመልከቱ)፡፡

አፄ ምኒልክ በስማቸው ገንዘብ እንዳሣተሙ በጎጃም አካባቢ ድጋፍ የሚሰጡ ግጥሞች ቀርበው ነበር፡፡ ከነዚህም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ነበሩ፡፡

ሀ. ትከሻየ ለምዶ መሸከም አሞሌ፤
መውጣት መውረዱ ሲወዘውዘኝ፤
እምዬ ምኒልክ ብር አሠራልኝ፡፡

ለ. አጋሰስ መጋጃ አህያ እንዳንጭን፤
ፈረንጅ በጥበቡ እንዳይኮራብን፤
እምዬ ምኒልክ ሠራልን ብሩን፡፡

ሐ. ከገበያ ወጡ ጥይት እና ጨው፤
የፈረንጅ ብር ሠራ የኛ አባ ዳኘው፡፡

መ. ዝቀህ ስጠኝና አሸከርህ ልክበር፤
ዳኘው ካስነጠርከው ከሠራኸው ብር፡፡

ከባንኩ መቋቋም በኋላ እ.ኤ.አ በ1932 በባንኩ በኩል በሁለት፣ በአምስት፣ በአሥር ፣በአንድ መቶ ፣በአምስት መቶ እና በአንድ ሺ ብር ሂሳብ የታተመ ባንክ ኖት የተባለ የገንዘብ ወረቀት ወጣ፡፡

ከላይ በተመሠረተው ውል መሠረት ዘመናዊ ባንክ በ1905 አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተቋቋመ፡፡ በዚህ ጊዜ ባንኩ የተሰጠው መጠሪያ የኢትዮጵያ ባንክ (Bank of Abyssinia) የሚል እንደነበር በውሉ ተገልጾአል፡፡ ካፒታሉ አምስት መቶ ሺህ ሲሆን በጊዜው ጥቅሙ በሕዝቡ ስላልታወቀ የሚገለገሉበት በአብዛኛው የውጭ ዜጎች ነበሩ፡፡ በኋላ ግን እ.ኤ.አ በ1917 የፈረንሳይ ወደብ ከነበረችው ጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ የባቡር መስመር መዘርጋት ለባንኩ ሥራ እንቅስቃሴ ይበልጥ እየረዳ መጣ፡፡ በዚህም የመጀመሪያዎቹ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ድሬዳዋ፣ ጎሬና ደሴ ተከፈቱ፡፡

አንድ ባንክ ሥራውን ሲጀምር ቅድሚያ የሚሰጠው ያለውን ገንዘብና ልዩ ልዩ የተከበሩ ማዕድናትን እንዲሁም በአደራ የሚቀበላቸውን ጌጣጌጦችና ወድ ቅርሶችን በጥንቃቄ የሚያስቀምጥበትን ቦታ በአስተማማኝ ሁኔታ ማሠራትን ነው፡፡ የአቢሲንያ ባንክም ይህንን ያሟላ ነበር፡፡

ወደባንኩ ምድር ቤት ወረድ ሲባልም እኔ ነኝ ያለ ጎበዝ በአንድ ዕጅ ሊያነቃንቀው የማይችል ከወፍራም ብረት የተሠራ በአምስት ቁልፍ የሚከፈት በር ይገኛል፡፡ ቁልፎቹ የሚገኙት በባንክ ተወካይ፣ በገንዘብ ሚኒስቴር ተወካይ፣ በቤተ መንግሥት ተወካይና በሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ታዛቢዎች ዕጅ ሲሆን ሁሉም በአንድነት ተገኝተው ይከፍቱታል፡፡ መጀመሪያ የባንክ ተወካይ ይከፍታል፤ እንዲያም ሆኖ ዘሎ ዘው አይባልም፡፡ ከቤተ መንግሥትና ከገንዘብ ሚኒስቴር ተወካዮች ዕጅ የሚገኙ ሁለት ቁልፎች ሁለተኛውን በር እንዲከፍቱ ይደረጋል፡፡ አሁንም አያበቃም፡፡ ብቻ ምን አታከተዎት አሥሩን ሲረግጡ ውለው ነው ከገንዘቡም ሆነ ከሌሎች ካዝናዎች የሚደርሱት፡፡

ከሁሉም የሚገርመው ሞተሩ ዛሬም ቢሆን በቃኝ ያላለው ያየር ማቀዝቀዣ (Air Conditioner) በሙቀት ምክንያት ብልሽት እንዳይደርስ የነበረውን ጥንቃቄ ማሳየት ብቻ ሳይሆን ግሊጋሎት ይሰጡ የነበሩ ቁሳቁሶች ሁሉ እንደዘመኑ መሣሪያዎች ብልጭ ብለው ድርግም የሚሉ ዓይነቶች እንዳልነበሩ ይጠቁማሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ይታይ የነበረው የአሠራር ጥንቃቄ ይበልጥ ሕዝቡን ወደ ባንክ እየሳበው ሄደ፡፡ ሰዎች ገንዘብ ለማንቀሳቀስ ሲፈልጉ የውጭ ዜጋ ለነበሩት የባንኩ አዛዦች ደብዳቤ ጽፈው ወደ እንግሊዝኛ በማስተርጎም ያቀርቡ ነበር፡፡

በዳግማዊ ምኒልክና የግብፅ ብሔራዊ ባንክ ተወካይ በነበሩት በሚስተር ማክጌልቨር መካከል በተካሄደው ስምምነት መሠረት በ500,000 ካፒታል በተጀመረው የባንክ ሥራ እንቅስቃሴ የተወሰነውን አክሲዮን(share) ይዘው የነበሩት የሎንደን፣ ፓሪስና ኒዮርክ አገር ሰዎች እንደሆኑ

በታሪክ ተዘግቧል፡፡ ባንኩ ሲቋቋም የክብር ጠባቂ አፄ ምኒልክ ነበሩ፡፡ እ.ኤ.አ በ1917 ንግሥት ዘውዲቱ ተኳቸው፡፡ ባንኩ እንደማንኛውም ባንክ ሁሉ ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ያቀርብ ነበር፡፡ (አባሪ ሁለትን ይመልከቱ)

**የኢትዮጵያ ባንክ**

ይህ ባንክ ለትርፍ ብቻ በመቆሙና ተገቢውን ግልጋሎት ባለመስጠቱ አፄ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣን እንደያዙ በሌላ ባንክ ለመተካት ተወሰነ፡፡ በዚህ መሠረት በእንግሊዝ በኮንትራት የሚንቀሳቀሰውን የአቢሲንያ ባንክ የኢትዮጵያ መንግሥት ገዛው፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ለባንክ መግዣ የሚሆን ገንዘብ ያገኘው ለሕዝቡ አክሲዮን (share) በመሸጥ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ለሽያጭ የቀረበው የአክሲዮን ክፍያ 30,000 ሲሆን የአንዱ ዋጋ 25 ፓውንድ ስተርሊንግ ነበር፡፡ በአክሲዮን ግዢው የተሳተፈው በአብዛኛው መንግሥት ነበር፡፡ ይህ ገቢ ባለቤትነትን ከአቢሲንያ ባንክ ወደ ኢትዮጵያ ባንክ ለማዘዋወር ለተጠየቀው ወጪ ተከፈለ፡፡ የተቋቋመው አዲሱ ባንክም ‹የኢትዮጵያ ባንክ› በሚል መጠሪያ ተሰየመ፡፡

የኢትዮጵያ ባንክ በአፍሪካ ውስጥ ሙሉ በሙሉ በአገሬው ተወላጆች የሚንቀሳቀስ የመጀመሪያው ባንክ ሆነ፡፡ የዚህ ባንክ ሌላ መጠሪያ ስሙ ‹የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ› የሚል ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ባንክ የተቋቋመው እንደአውሮጳውን የዘመን አቆጣጠር ነሐሴ 29 ቀን 1931 በወጣው ዐዋጅ ሲሆን መነሻ ካፒታሉ 7500 ፓውንድ ስተርሊንግ ነበር፡፡

አፄ ኃይለ ሥላሤና የገዢው መደብ መሣፍንት የአክሲዮን ተካፋይ ከመሆን የሚገኘውን ትርፍ በወቅቱ ጠንቅቀው ያውቁ ስለነበር የውጭ ድርጅቱን ካምፓኒ ለመግዛትና በኢትዮጵያ ባንክ ለመተካት አክሲዮን ገዙ፡፡ በዚህ መሠረት ባንኩን ከነቅርንጫፎቹ በመግዛት መሣፍንቱ የኢትዮጵያ ባንክ ባለቤቶች ሆኑ፡፡

አዲሱ ባንክ የአቢሲንያን ባንክ ሥራ በመተካት እና ቢሮውን በመረከብ የንግድ ሥራውን በጀመረበት ወቅት የወረቀት ገንዘቦችን እና ሳንቲሞችን የማተም ሥልጣንም ነበረው፡፡ በድሬ ዳዋ፣ በጎሬ፣ በደሴ፣ በደብረ ታቦርና ሐረር ቅርንጫፎች፣ እንዲሁም በጋምቤላ በወኪል እና በጅቡቲ የሐዋላ ቢሮ(Transit Office)ነበረው፡፡

በመጨረሻም ገንዘብን በአስተማማኝ ሁኔታ በማስቀመጥ ባንኩ የሚሰጠው አገልግሎት በሕዝብ ዘንድ እየታወቀ በመሄዱ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የሚሰጠው ጠቀሜታ አደገ፡፡ ባንኩ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ባንክ ከመሆኑም ባሻገር የኢትዮጵያውያንን ጥቅም ለማስከበር ከልብ የቆመ ነበር፡፡

ሕዝቡ የባንክን ጥቅም ከተረዳ በኋላ ኑሮውን ለማሻሻል አቅሙ በፈቀደለት መጠን የቤት መሥሪያ ይበደር እንደነበር ታሪክን ለመጠበቅ አደራ ከተቀበሉ ማህደሮች ውስጥ የተገኘው ይህንን ይመስላል፡፡

ከ1905 እስከ 1936 በነበሩት ጊዚያት አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ ባንኮች

| **የተከፈተበት ዘመን** | **የባንኩ ስም** |
|---|---|
| 1905እ.ኤ.አ | Bank of Abyssinia |
| 1908 እ.ኤ.አ | Societe 'Ethiopia Pourle Development de'l Agriculture et du Commerce |
| 1915/እ.ኤ.አ | Banque del'Indochive |
| 1915 /እ.ኤ.አ | Compagnie del Afrique Oriential |
| 1931 /እ.ኤ.አ | Bank of Ethiopia |

የኢትዮጵያ ባንክ እስከ 1935 አገልግሎት ሲሰጥ ከቆየ በኋላ ፋሽስት ኢጣሊያ አገሪቷን በወረረበት ጊዜ ሥራው ሊቆም ችሏል፡፡ ከዚያም ጠላት ለአምስት ዓመት ያህል በቆየበት ጊዜ የሚከተሉትን ባንኮች ከፍቶ ነበር፡፡ እነዚህም፡-

- Banco di Italia
- Banco di Roma
- Banco di Napoli
- Banco di Nationali del Lavoro
- Cassa di Credits
- Agrasee Minerario

Societ a Nazionale di Ethiopia

የእነዚህ ባንኮች ቅርንጫፎች በአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች በ37 ቦታዎች ሲሠሩ ከቆዩ በኋላ ጠላት ድል ተመትቶ የኢትዮጵያ ነፃነት እውን እንደተደረገ ባንኮ ዲ ሮማ እና ባንኮ ዲናፖሊ ብቻ በአሥመራ፣ በምፅዋና አሰብ ግልጋሎታቸውን ቀጠሉ፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ እ.ኤ.አ በ1942 ተቋቋመ፡፡ ባንኩ መነሻ ያደረገው የገንዘብ መጠን 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን) ጠገራ ብር ነበር፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ 43 ሠራተኞችን ይዞ ቀደም ሲል የአቢሲንያ ባንክ እየተባለ ይጠራ በነበረው ሕንፃ ውስጥ ሥራውን ጀመረ፡፡ ከዚህ በኋላ የንግድና የማዕከላዊ ባንክ ሥራዎች ቀድሞ ከነበረው ተስፋፍተው ቀጥለዋል፡፡ ባንኩ ገንዘብ የማሣተም፣ የአገሪቱን የውጪ ምንዛሬ የመቆጣጠርና የመንግሥት የገንዘብ ወኪል ሆኖ የመሥራት ሥልጣን ነበረው፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ እየተጠናከረ ከመጣ በኋላ ቅርንጫፎቹን በአንዳንድ ዋና ዋና ከተሞች በመክፈት የባንክ አገልግሎት በመጠኑ እንዲታወቅ አድርጓል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የሥራ እንቅስቃሴውን በማስፋፋት ሕዘቡ በቁጠባ ሂሳብ መጠቀም ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አስተዋውቋል። በዚህ ብቻ አልተወሰነም። ባደገ ቁጥር በተለይም የእንግሊዝ ወታደሮች ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ተከፍቶ የነበረው እና ለሁለት ዓመት ግልጋሎት የሰጠው ባርክሌይ ባንክ እና ዴሌ ኢንዶቺና በሀገሪቱ ባንክ ደንብ መሠረት እንዲዘጉ ተደርጓል።

እ.ኤ.አ በ1963 ሥራውን እስካቆመበት ጊዜ ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ በ28 ዋና ዋና ከተሞች ቅርንጫፎቹን የከፈተ ሲሆን በካርቱም እና በጅቡቲም ቢሮዎች ነበሩት። በዚያን ወቅት የሠራተኞቹ ቁጥር 902 ደርሶ እንደነበርና በተለይም ዛሬ ላለው የባንክ ሥራ እንቅስቃሴ ጥሩ መሠረት እንደጣለ ይነገርለታል።

እ.ኤ.አ ጁላይ 1963 በአዲሱ የገንዘብ እና የባንክ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ በዐዋጅ ወደ ብሔራዊ ባንክ እና ንግድ ባንክ ተከፈለ።

ያለፉትን ዘመናት በተለይም በደርግና ከዚያም በፊት የነበሩትን መንግሥታት የባንኮች መቋቋም ዕድገት ስንመለከት ቁጥራቸው በፈጣን ሁኔታ እየጨመረ መሄድ የሚታይበት አልነበረም። ከ1983 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ በኋላ ግን በርካታ ባንኮች ተቋቁመዋል፤ አህንም በምሥራታ ላይ እንዳሉ በማስተዋወቅ ላይ የሚገኙ አሉ። እስካሁን ባለን መረጃ መሠረት ባለፉት ሁለት አሠርት ዓመታት ውስጥ ብቻ የሚከተሉት የግል ባንኮች በሀገራችን ተመሥርተው ሕዝቡን በማገልገል ላይ ናቸው። እርግጥ ነው በ85 ሚሊዮን ሕዝብ መካከል የ15ና 20 ባንኮች መገኘት አባይን በጭልፋ ዓይነት ነው። የሀገራችን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በፍጥነት ማደግ የሚችልበት ዕድል አሁን ካበት አበረታች ሁኔታ ይበልጥ ተመቻችቶ ከቀጠለ እነዚህ እፍኝ የማይሞሉ ባንኮች የሕዝቡን የባንክ አገልግሎት ጥማት ሊያረኩ እንደማይችሉ ግልጽ ነው። ለምሳሌ የኢትዮጵያን ሕዝብ ግማሽ የማይሆነውን የኬንያን ሕዝብ የሚያገለግሉትን የግል ባንኮች ብናይ ቁጥራቸው 44 ነው(በ2009 እ.አ.አ የኬንያ ሕዝብ 39,802,015 እንደነበር ከጉግል መመልከት ይቻላል)። ከዚህ አንጻር የኞቹ በጣም ኢምንት ናቸው ማለት እንችላለን። ለማንኛውም ካሉን የመንግሥት ባንኮች ጎን ለጎን የሚከተሉት የግል ባንኮች በሀገር ልማት ረገድ የበኩላቸውን አወንታዊ ሚና እየተጫወቱ እንደሚገኙ ልንገነዘብ ይገባል።

1. አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ
2. አቢሲንያ ባንክ
3. ዳሽን ባንክ
4. ወጋገን ባንክ
5. ኅብረት ባንክ
6. ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ
7. ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ
8. ዴቨሎፕመንት ባንክ ኦፍ ኢትዮጵያ
9. አንበሣ ኢንተርናሽናል ባንክ
10. ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ
11. ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ
12. ኮኦፐሬቲቭ ባንክ ኦፍ ኦሮሚያ
13. ኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ
14. ዘመን ባንክ
15. እናት ባንክና ሌሎችም በምሥረታ ላይ ያሉት ይገኙበታል።

የባንኮችን ሰያሜ በተመለከተ አንዳንዶች ከታሪክ ጋር ቁርኝት ያላቸው ይመስላል። ለምሳሌ "አቢሲንያ ባንክ"ን ልብ ይሏል።

የባንኮችን ሪፖርት ለማሻተት ስንሞክር በአብዛኛው ውጤታማ እንደሆኑና ጠቀም ያለ ትርፍ እንደሚያስመዘግቡ ይነገርላቸዋል። ከዚህ ነጥብ ጋር በተያያዘ ልክ እንደሌሎች ያደጉ ሀገሮች ባንኮች በኪሣራ የተዘጋ ባንክ በሀገራችን እንደሌለ ስንሰማ በእርግጥም መስኩ አዋጭነት እንዳለው መረዳት እንችላለን።

በአጠቃላይ ባንክ ለሰው ልጅ እጅግ ጠቃሚ ከሆኑ የገንዘብ ተቀቋማት መካከል ዋነኛው ነው ማለት እንችላለን። ከዚህ ዓለማቀፋዊ በረከት ወይም ትውፊት መሣተፍ የቻልነው በቅርቡ ቢሆንም (ገና አንድ መቶ ዓመት ገደማ ነው) በተለይ በአፄ ኃይለ ሥላሤና በቀጣዩ የደርግ መንግሥት ለብዙ ዓመታት አገልግሎቱ ሲንቀራፈፍ ቆይቶ ባለፉት ጥቂት አሠርት ዓመታት ግን በአንጻራዊ ሁኔታ እመርታ ያሳየበት ሁኔታ ይስተዋላል። ይህ ይበል የሚያሰኝ የባንኮችና ተያያዥ የመድን ዋስትና ተቋማት ዕድገት ዘመኑ በሚፈቅደው ዓለም አቀፍ የባንኮችና የኢንሹራንስ ሕግና ደንብ መሠረት ይበልጥ እንዲያድግና እንዲመነደግ በዚያውም በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖረው የሀገራችን ሕዝብ ከእስከዛሬው በበለጠ የመስኩ ተጠቃሚ የሚሆንበት ዕድል እንደሚመቻች ተስፋ በማድረግ ይህችን በኢትዮጵያ የባንኮች አመሠራረት ዙሪያ ያጠናቀርኳትን አነስተኛ ጽሑፍ እቋጫለሁ።

### ይህን ያውቁ ኖረዋል?

ቀደም ባለ አንድ ወቅት እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ አንድ ባለፀጋ ሰው ነበሩ — ታሪኩ በስፋት የሚታወቅ ቢሆንም ስም መጥራት አያስፈልግም። የባንክ አገልግሎት ገና እምብዝም ባልተለመደበት በዚያን የቆዩ ዘመን የባንክ ደንበኛ ኖረዋል። ጧት ጧት ወደባንኩ እየሄዱ ታዲያ ከባንኩ ዘበኞች አንዱን በሹልክታ ይጠሩና ስለባንኩ በደህና ማደር ከጠየቁና በ‹ሰላም ማደሩን›ም ከተረዱ በኋላ የሻይ ብለው ይሄዱ ነበር አሉ። የአሁን ዘመን ሰው ብልጥ ነው — ኃላፊነቱን ለባንክ ጥበቃዎች ሰጥቶ ለጥ ብሎ ይተኛል። ነውር አይደለም?

# አባሪ አንድ

እኔ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያና የምስር አገር ባንክ ቀጥሎ በተጻፈው ውል ተዋውለናል።

መጀመሪያ ውል

የምስር አገር ባንክ የባንክ ኩምፓኒ ሰብስቦ የባንኩን ሥራ አበጅቶ ባንኩን በኢትዮጵያ ይቆማል። ባንኩም የኢትዮጵያ ባንክ ይባላል። የኩምፓኒውም ዋና ገንዘብ አምስት መቶ ሺ ጊኒ ነው። በመጀመሪያ መቶ ሺ ጊኒ ተይዞ የባንኩን ሥራ እንጀምራለን። የቀረውን አራት መቶ ሺ ጊኒ በተፈለገ ጊዜ ይገባል። ይህም አምስት መቶ ሺ ጊኒ ለባንኩ ሥራ የሚያንስ የሆነ እንደሆነ ይጨምራሉ። ከነጋሥታቱም እስከ ፈቅደው በለንደን በፓሪስ በኒዮርክ በበርሊን በሮማ በቤና በምስር በአዲስ አበባ ከዚህ ከኢትዮጵያ ባንክ የወደደ ሰው ሁሉ አክሲዮን እንዲገዛ ይከፋፈላል። የባንኩም ዋና ቦታው አዲስ አበባ ላይ ይሆናል። ይህም ባንክ በኢትዮጵያ በሌላም አገር ባንክ ከወደደበት ቦታ ላይ ወኪል ያስቀምጣል። ሥራ ከሚጀመርበት ቀን አንስቶ እስከ አምሳ ዓመት ይህ የባንክ ፈቃድ ለዚህ ለኢትዮጵያ ባንክ ብቻ ተፈቅዷል።

፪ተኛ ውል

ሥራ ከሚጀመርበት ቀን አንስቶ እስከ አምሳ ዓመት ድረስ ቀጥሎ የተጻፉትን ስምንት ክፍሎች ለኢትዮጵያ ባንክ ብቻ ተፈቅደዋል።

፩ኛ ክፍል

የኢትዮጵያ መንግሥት ሌላ ባንክ ለማቆም ውል አይሰጥም።

፪ተኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ባንክ ብቻ የኢትዮጵያን የገንዘብ ወረቀት ያትማል። ይህም የገንዘብ ወረቀት ደምበኛ ገንዘብ ነው። መለወጥ የፈለገው ሰው በብር ወይም በወርቅ እንደወደደ አዲስ አበባ ላይ ይለውጣል።

፫ኛ ክፍል

መንግሥት ብር አያሳትምም። የኢትዮጵያ ባንክ ብቻ ትርፉን እንዲወስድ ከመንግሥት እየተማከረ ያሳትማል።

፬ተኛ ክፍል

የመንግሥት ግምጃ ቤት ብርና ወርቅ ሁሉ ከኢትዮጵያ ባንክ ይቀመጣል። የኢትዮጵያም መንግሥት ለየጉዳዩ የሚሰጠው ገንዘብ በቼክ ይወጣል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ገንዘብ መበደር የፈለገ እንደሆነ ብድሩን ይኸ ባንክ ይፈልጋል። ለዚህ ለኢትዮጵያ ባንክ ሳይማከር የኢትዮጵያ መንግሥት ከሌላ ባንክ ብድር አይፈልግም። ይህ ባንክ ግን ብድሩን አላገኘም ያለ እንደሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት ብድሩን ከሌላ ዘንድ መፈለግ ይችላል። የብድሩ ውል የኢትዮጵያ ባንክ ከሚሰጠው ያነሰ እንደሆነ በዚህ ጊዜው የብድር ውል ከኢትዮጵያ ባንክ የኢትዮጵያ መንግሥት ይበደራል። የኢትዮጵያ ባንክ እልቻልም ያለ እንደሆነ ግን የኢትዮጵያ መንግሥት ከሌላ ዘንድ መበደር ይችላል።

፭ኛ ክፍል

ለሰዋስ የተያዘ የነጋዴ ዕቃ ማስቀመጫ ታላላቅ ቤት የኢትዮጵያ ባንክ እንዲሰራለ ተፈቅዶለታል።

፮ተኛ ክፍል

ለኢትዮጵያ ባንክ ለወኪሎቹ የዋና ባንክ ቤትና ለሰዋስ የተያዘውን የነጋዴ ዕቃ ማስቀመጫ ቤት የሚሰራበት ቦታ በየከፍራው መንግሥት እሰዋጋ ይሰጣል።

፯ኛ ክፍል

በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የኢትዮጵያ ባንክ ብርና ወርቅ በመንግሥት ከራይ ልክ በምድር ገሩር ይጫናል።

፫ኛ ውል

የኢትዮጵያ ባንክ ከትርፉ ከሚያውቁና ከመቶ አስር መጠባበቂያ እንክቶ ደግሞ ለባለ አክሲዮን ለመቶ ብር ሰባት ብር ወለድ ሰጥቶ ከቀረው ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከመቶ ሃያ ይሰጣል።

፬ኛው ውል

ይህ የኢትዮጵያ ባንክ ኩምፓኒ የባንኩን ሥራ በ፲፰፻፺፯ ዓመተ ምሕረት በነሐሴ በ፳፬ ቀን ያልጀመረ እንደሆነ ይህ የተዋዋልነው ውል ይፈርሳል። ይህ ውል በትክክል ሁኖ ከሁለት ቦታ ተጽፎ አንዱ ለኢትዮጵያ መንግሥት አንዱ ለምስር ባንክ እንዲ ይቀመጣል። መጋቢት ፩ ቀን ፲፰፻፺፯ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ።

## ክፍል ሁለት

| | 1916 | | 1917 | | 1918 | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | Debit | Credit | Debit | Credit | Debit | Credit |
| Cash . . . . . . . | £ 1,355,738 | £ 1,360,309 | £1,501,190 | £ 1,517,562 | £ 2,210,065 | £ 2,173,434 |
| Guaranteed advances . . . . . . . | 70,116 | 52,651 | 98,329 | 92,743 | 112,667 | 107,927 |
| Current accounts . | 718,415 | 722,270 | 837,053 | 750,526 | 1,066,122 | 1,070,489 |
| Advances against merchandise. . . | 139,596 | 154,057 | 221,004 | 205,774 | 428,309 | 363,884 |
| Bills discounted . . | 79,024 | 90,973 | 30,562 | 28,448 | 90,067 | 84,702 |
| Advances against Securities . . . . | 439 | 782 | 84 | 599 | 1,807 | 6,993 |
| Foreign Bills . . . | 92,248 | 94,706 | 224,981 | 221,763 | 345,991 | 352,396 |
| Local Bills . . . . | 82,364 | 81,822 | 55,545 | 55,417 | 93,719 | 93,897 |
| Deposits . . . . . | 594,194 | 593,318 | 999,501 | 1,037,116 | 1,705,858 | 1,787,049 |
| Fixed Deposits . . | 113,001 | 109,973 | 110,268 | 115,535 | 132,125 | 152,850 |
| | £ 3,245,135 | £ 3,260,864 | £ 4,078,817 | £ 4,025,483 | £ 6,186,730 | £ 6,193,621 |

N.B. — For the purpose of comparison between the different years, the conversion of dollars included in the above table has been made at the rate of $ 10 per £stg.

**Bank Notes.** — The issue remains at its original figure of $ 214,765, fully covered by coin. The amount in circulation in the hands of the public at 31st December 1918 was $ 130,715 against $ 149,140 at the same date in 1917.

**Imports and Exports.** — The following statistics of exports from Djibouti are published by the *Journal Officiel de la Côte Française des Somalis*:

| | 1916 | 1917 | 1918 |
|---|---|---|---|
| Hides (in kilos) | 4,042,551 | 5,704,423 | 9,190,674 |
| Coffee » | 4,520,279 | 5,092,647 | 3,056,875 |
| Beeswax | 482,091 | 381,313 | 146,446 |

As relating to the Western Districts of Abyssinia, we are indebted to the Sudan Government for the following figures:

Exports from Abyssinia to the Sudan and in transit through the Sudan.

| | 1916 | 1917 | 1918 |
|---|---|---|---|
| Coffee . . . . . . . . . . . . . . | L. E. 68,912 | L. E. 105,895 | L. E. 155,102 |
| Beeswax . . . . . . . . . . . . . | » 20,751 | » 18,265 | » 10,874 |
| Miscellaneous . . . . . . . . . . | » 7,742 | » 8,764 | » 26,456 |
| TOTAL . . . | L. E. 97,405 | L. E. 132,924 | L. E. 192,432 |

Imports into Abyssinia from the Sudan and in transit through the Sudan.

| | 1916 | 1917 | 1918 |
|---|---|---|---|
| Salt and Sudan products . . . . | L. E. 7,497 | L. E. 16,239 | L. E. 17,194 |
| Cotton goods, silks, &c. . . . . . | » 27,892 | » 37,713 | » 77,663 |
| Miscellaneous . . . . . . . . . . | » 2,171 | » 11,274 | » 18,728 |
| TOTAL . . . | L. E. 37,560 | L. E. 65,226 | L. E. 113,585 |

The Director retiring this year is H.E. the Fitaurari HAPTE GHIORGHIS, who offers himself for re-election.

In terminating, we desire to place on record our appreciation of the zealous service performed by our staff in Abyssinia during the past year, and to thank Mr. Collier, the Governor of the Bank in Abyssinia, for his unflagging care for the interests of our institution.